# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 75 ጥቅምት 12 2002 ዓ.ም ገጽ 1


**ማስታወቂያ**

**የግንቦት 7 ድምጽ ከጥቅምት 15 ቀን 2002 ጀምሮ የአየር ሞገድ ለውጥ በማድረግ በተመሳሳይ ሰዓትና ቀናት በ7530 kHz በ41 ሜትር ባንድና በ9610 kHz በ31 ሜትር ባንድ ላይ የሚተላለፍ መሆኑን እናስታውቃለን። የግንቦት 7 ድምጽ**

## በመከላኪያ ሚንስቴር የመንግሥት ገንዘብ ዘረፋ ተጧጡፎአል

የመከላከያ ሚኒስትር ባለስልጣናትና የወየኔው ጀኔራሎች እንደልባቸው ለወሰዱት ገንዘብ በሂሳብ ማወራረጃ ሰነዱ ላይ አንፈርምም በማለታቸው፣ የሂሳብ ሰራተኞቹ ጨንቀት ውስጥ መግባታቸውን የደረሰን መረጃ አመለከተ።

ጄኔራሎቹ እስካሁን ድረስ ለወሰዱት የህዝብ ገንዘብ ፊርማቸውን እንዲያኖሩ በሂሳብ ሰራተኞች ቢጠየቁም ፣ ጄኔራሎቹ ግን የእኛን መስሪያ ቤት ኦዲት ለማድረግ የሚችል አንድም ሰው በራችን ላይ ዝር አይልምና አትፍሩ ብለው መመለሳቸውን ከመከላከያ ያገኘነው መረጃ አመልክቷል።

የሂሳብ ሰራተኞቹ በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ ጭንቀት ውስጥ መግባታቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ ከሀላፊነታቸው ለመልቀቅ ቢፈልጉም በጥብቅ ቁጥጥር ስር በመገኘታቸው ለመልቀቅ እንዳልቻሉ ምንጮች አስረድተዋል።

የወያኔ ወታደራዊ መኮንኖች እንደልባቸው በሚያወጡት ገንዘብ የግል መኖሪያ ቤቶችንና የንግድ ድርጅቶችን እንደሚገዙ ቀደም ብሎ በግንቦት 7 ድምጽ መዘገቡ የሚታወስ ሲሆን፣ ከዘገባው በሁዋላም ዝርፊያው ተጠናክሮ መቀጠሉን ከስፍራው የሚደርሱን መረጃዎች ያመልከታሉ።

የወያኔ የመከላከያ ባለስልጣናት ገለልተኛ ኦዲተር የሚባል ነገር በመስሪያ ቤቱ ዝር እንዳይል በማድረጋቸው፣ ለአመታት የተወዘፈው በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር የህዝብ ገንዘብ እስከዛሬ ድረስ ኦዲት ሊደረግ አለመቻሉንም መረጃው ያመለክታል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ወያኔ በየአመቱ ለሲቪል ሰራተኞች የሚሰጠው የፖለቲካ ስልጠና ምንም ውጤት ውጤት እንዳላመጣ ሰራተኞች ገለጹ

የግንቦት 7 ዘጋቢ ተዘዋውሮ ያነጋገራቸው ሰራተኞች እንደተናገሩት፣ ከ1996 ዓም ጀምሮ ለሰራተኛው የሚሰጠው የፖለቲካ ስልጣና ምንም ውጤት ሊያመጣ አልቻለም። አንድ ስማቸው አንዳይገለጽ የፈለጉት ር'ዕሰ መምህር ለግንቦት 7 ዘጋቢ እንደገለጹት በያመቱ " በእንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ፣ በገጠር ልማት ፖሊሲዎች ስልቶች፣ የውጭ ጉዳይና የአገር ጉዳይ ፖሊሲዎች ስትራቴጂ፣ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታና የማስፈጸም አቅም ግንባታ" በሚሉ አበይት ርእስጉዳዮች ዙሪያ ላለፉት 5 አመታት ለመምህራንና ለሰራተኞች የፖለቲካ ትምህርት ቢሰጥም፣ ሰራተኛው ግን አሁንም ለወያኔ ያለውን ጥላቻ ከመግለጽና ስልጠናውም ውጤት አለማምጣቱን ከመናገር አልተቆጠበም።"

መምህራንም ሆኑ ሌሎች ሰራተኞች ስልጠናውን የሚወስዱት የውሎ አበል ለመቀበል ፣ ከስራ ላለመባረር ወይም የደረጃ እድገት ለማግኘት ሲሉ መሆኑን የሚናገሩት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰራተኞች ፣ ወያኔ ግን አሁንም ድረስ ከፍተኛ የሆነ የአገር ሀብት እያባከነ ስልጠናውን ከመስጠት አልተቆጠበም" በማለት ያማርራሉ። የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ዘንድሮ ስልጠናውን የወሰዱት በፍቼ ከተማ ሲሆን፣ ወያኔ ከፍተኛ ወጭ አውጥቶ ካሰለጠነ በሁዋላ መምህራኑን የአባልነት ፎርም እንዲሞሉ ሲጠይቃቸው ዘወር በል ብለው እንደመለሱለት ለማወቅ ተችሎአል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## የኦጋዴን ነጻ አውጭ ድርጅት በወያኔ የሰሞኑ ድራማ ላይ መሳለቁን ገለጸ

ወያኔ ሰሞኑን እንደልቡ በሚቆጣጠረው ቴሌቪዥን የኦጋዴን ነጻ አውጭ ድርጅት መሪ እጁን መስጠቱንና ግምባሩ ይጠቀምባቸው የነበሩ በርካታ መሳሪያዎችም መያዛቸውን በመግለጽ ያቀረበው ዘገባ ከእውነት የራቀ መሆኑን ግምባሩ ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ አስታውቋል።

የወያኔ ቴሌቪዥን ከአራት ቶን በላይ ለፈንጂ መስሪያ የሚውሉ ቁሳቁሶችንና፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ጥይቶችን መያዙን ቢያስታውቅም፣ ግምባሩ ግን ወያኔ በተደጋጋሚ በቴሌቪዥን የሚያቀርባቸው ሰዎች ራሱ የፈጠራቸው ናቸው ሲል የወያኔን ፕሮፓጋንዳ አጣጥለውታል።

"ወያኔ ምንጊዜም የድል ዜናዎችን መስማት ይመኛል፣ ይህን ምኞቱን ለማሳካትም እንደዚህ አይነቶችን የፈጠራ ዘዴዎች ይጠቀማል" የሚለው የግምባሩ መግለጫ፣ የግንባሩን መልካም ስም ለማጉደፍም ወያኔ በርካታ ዘዴዎችን እየተጠቀመ ነው ብለዋል። በተለይ ግምባሩን አልሻባብ **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## በአዲሱ "ወይ'ን ለመኖር" ፖሊሲ ህዝቡ ምሬቱን እየገለጸ ነው በኦሮሚያ ከ10 ሺ በላይ ሰዎች ከሥራ ተባረሩ

"ወይ'ን ለመኖር" ተብሎ የሚጠራውና በቅርቡ በሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተግባራዊ እየተደረገ ያለው ፖሊሲ ህዝቡን በከፍተኛ ደረጃ እያነጋገረ ምምጣቱን ሪፖርተራችን ዘግቧል። "ወይ'ን ለመኖር" የሚባለው ፖሊሲ ዜጎች ስራ ለመቀጠር ወይም እርዳታ ለማግኘት የወያኔ አባል እንዲሆኑ የሚያስገድድ ሲሆን፣ ይህን የአባልነት ፎርም ያልሞሉ ሰራተኖች ከስራ እየተባረሩ በምትካቸውም የአባልነት ፎረም የሞሉ አዲስ የወያኔ ተሿሚዎች እየገቡ ነው።

ከዩኒቨርስቲ የተመረቁ ወጣቶችም ስራ ለማመልከት ሲሄዱ የአባልነት ፎርም በቅድሚያ እንዲሞሉ እንደሚጠየቁ የገለጸው ዘጋቢያችን፣ ሰሞኑን በኦሮሚያ ክልል በግምገማ የተባረሩትን ከ9 ሺ በላይ ሰራተኞችን ለመተካት አዲስ ክፍት የስራ ማስታወቂያ በ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ቢወጣም፣ ተመራቂ ተማሪዎቹ ስራ ለማመልከት በሄዱበት ጊዜ የገጠማቸው የስራ ምዝገባ ሳይሆን "ወይ'ን ለመኖር" የተባለው ቅጽ እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል። ተማሪዎች ለምዝገባ ሲሄዱ "የኢህአዴግን የልማት ፖሊሲ መቀበላችሁንና **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## አምንስቲ ኢንተርናሽናል የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ብርቱካን ሚደቅሳን ለማስፈታት ዓለም አቀፍ ዘመቻ ጀመረ

በዘረኛው እና ሓላቀሩ የወያኔ ቡድን በግፍ ታስራ የምትማመቅቀውን የአንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ ሊቀመንበር ብርቱኳን ሚደቅሳን ለማስፈታት ታዋቂው የሰብአዊ መብት ተሟጋች የአምኒሲቲ ኢንተርናሽናል የሆላንድ ቅርንጫ ዘመቻ መጀመሩ ታወቀ።የኢትዮድያ ሚዲያ መድረክ ድረ ገጽ በምጽሀሩ ኢ ኤም ኤፍ የሆላንድ አምንስቲ ኢንተርናሽናል አባላት ለአውሮፓ ህብረት የሚሰጥ ፊርማ እያሰባሰቡ መሆኑን ዘግቧል። የሰብአዊ መብት ተሟጋቹ ድርጅት የሆላንድ ቅርንጫፍ አባላት የፊርማ ማሰባሰቡ ሂደት እስከሚያበቃበት ህዳር ሀያ ሁለት ሁለት ሺህ ሁለት አንድ ቀን በፊት በርካታ ፊርማዎችን ለማሰባሰብ እየተንቀሳቀሱ እንደሆነ ታውቋል። የአንድነት ለፍትህ እና ዴሞክራሲ ሊቀመንበር ብርቱኳን ሚደቅሳን ግርማ ሞገስ ያላት መሪ ሲል የገለጻት የኢትዮድያ ሚዲያ መድረክ የነጻነት እና የፍትህ ታጋይዋን የፋሺስቱ መለሰ ዜናዊ ብድን ለብቻዋ ማሰሩ እና የእድሜ ይፍታሽ ብያኔ ማሳለፉ ተያይዞ ቀርቧል።

ለአዲሱ የአውሮፓ ህብረት የልማት እና የረድኤት ኮሚሽነር ካርል ዴጉግት የሚላከው ደብዳቤ ላይ ኢትዮድያዊያን እና ማናቸውም ነጻነት እና ሰብአዊ መብት ወዳድ የምድር ዜጎች ሁሉ እንደፈርሙበት በድረ ገጹ ቀርቧል።ደብዳቤው ኮሚሽነሩ ብርቱኳንን ለማስፈታት በኮሚሽኑና በአባል አገራት አቅም ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ዓይነት ዲፕሎማሲያዊ ጫና እንዲያደርጉ የሚጠይቅ መሆኑ ታውቋል።

የኢትዮድያ ህዝብ ከዘረኛ እና ከዘረፊዎች ጋር የሚያደረገው እልህ አስጨራስ መራራ ትግል ጥቂት የማይባሉ አለምአቀፋዊ ወዳጆች እንዳፈራለት ግልጽ ነው። የአሚኒሲቲ ኢንተርናኘሽናል ሆላንድ ቢሮውም ለዚህ ትልቅ አብነት መሆኑን እንቅስቃሴው ይመሰክራል ተብሎአል። የሰብአዊ መብት ተሟገቹን እንቅስቀናሴ በርካታዎች ይደግፉታል ተብሎ እንደሚጠበቅ ተያይዞ የደረሰን መረጃ አመልክቷል።

## አንድ የወያኔ ባለስልጣን ከድቶ አሜሪካ መግባቱ ታወቀ

ሰይፈ ስዩም የተባለው በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን የስልጠናና ትምህርት ክፍል ዳይሬክተር የነበረው የወያኔው ሹመኛ፣ ለስልጠና ወደ አሜሪካ አገር ተልኮ በዚያው መቅረቱን ምንጮቻችን ገለጹ።

በድርጊቱ የተበሳጩት የወያኔ ሹማምንትም ባለስልጣኑ ወደ አገሩ በአስቸኳይ እንዲመለስ ትእዛዝ ያስተላለፉ መሆናቸው ሲታወቅ፣ ዳይሬክተሩ ግን ማስፈራሪያውን ወደ ጎን በማለት በአሜሪካን አገር ጥገኝነት መጠየቁ ታውቋል።

በቅርቡ የወያኔ ባለስልጣናት በሬዲዮና በቴሌቪዥን ጋዜጠኞች ላይ ከፍተኛ ግምገማ ማድረጋቸውንና እርስ በርስ መሻኮታቸውን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን፣ ጋዜጠኞችም ከህዝቡ የሚደርስባቸውን ጥላቻና ነቀፌታ መቋቋም አቅቷቸው ስራቸውን በገፍ እየለቀቁ አንዳንዶች ስደትን ሲመርጡ ሌሎች ደግሞ በግል ድርጅቶች እየተቀጠሩ መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል።

የወያኔ ሹማምንት በሬዲዮና በቴሌቪዥን የሚቀርበው ፕሮፓጋንዳ ህዝቡን ያሰለቸው ጋዜጠኞች ስራቸውን በተገቢው መንገድ ስለማይሰሩ ነው የሚል ክስ በጋዜጠኞች ላይ ማቅረባቸው የታወቀ ሲሆን፣ ጋዜጠኞች ደግሞ በበኩላቸው ህዝቡ በወያኔ አገዛዝ በመማረሩና የሚጨበጥ ስራ ባለመታየቱ ነው የሚጠላን የሚል መልስ መስጠታቸው ታውቋል።

ወያኔ ጋዜጠኞችን ጋዜጠኖች ደግሞ ወያኔን ተጠያቂ እያደረጉ ሲሆን ህዝቡ ግን ሁሉንም አንክሮ እንደተፋቸው የውስጥ ምንጮችን ጠቅሶ ሪፖርተራችን ከስፍራው ዘግቧል።

ህዝቡ በቀን አንድ ዳቦ በልቶ ማደር እየተሳነው ሚሊየነር ስለሆኑ አርሶአደሮች የሚዘግቡት የወያኔ ጋዜጠኞች፣ ህዝቡ ከጥላቻው መብዛት የተነሳ ከማህበራዊ ግንኙነት ሳይቀር እያገለላቸው እንደሚገኝ ታውቋል።

# ረሃብ ጊዜ አይሰጥም፤ ወገኖቻችንን ለመታደግ፣ ወያኔን ለማስወገድ እንጣደፍ

በሕዝባችን ላይ አስከፊ ረሃብ እየመጣ ነው። ድርቅን ተከትሎ ደግሞ የውሃ መጥለቅለቅም ሊኖር ይችላል የሚል ሥጋት አለ። እየመጣ ያለው ችጋር ስፋትና ጥልቀት በ70ዎቹና 80ዎቹ ከነበሩትም የባሰ ሊሆን ይችላል ተብሎ ተፈርቷል። ከአሁኑ ሰው በረሃብ መሞት መጀመሩ ከአራትና አምስት ወራት በኋላ የሚመጣውን አደጋ ከባድነት መገመት ያስችላል።

"ለስድስት ተከታታይ ዓመታት ከአስር በመቶ በላይ የኢኮኖሚ እድገት አሳይተናል" የሚለው ዓይን ያወጣ ውሸት፤ "ድህነትን ተረት እናደርጋለን" የሚለው ጉረኛ መፈክር፤ የወያኔዎችና ጀሌዎቻቸው በፎቅና ቪላዎች መንበሽበሽ፤ ለም መሬቶች በአበባ እርሻዎች መተካታቸው እና የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ራድዮ "የህዳሴ ብስራቶች" ለሕዝባችን ምሳና እራት አልሆኑም።

የረሃቡ ስጋት እየገፋ ሲመጣ መለስ ከአፄ ኃይለሥላሴም ሆነ ከኮሎኔል መንግሥቱ በባሰ ተፈጥሮ ላይ ማላከኩን ተያይዞታል። ለመሆኑ ተፈጥሮ ብቻውን እየተደጋገመ ለሚመጣ ችጋርና ቸነፈር በቂ ምክንያት ሆኖ ያውቃልን? ለምንድነው ፍትህና ነፃነት በሰፈነባቸው አገሮች ውስጥ ዝናብ ጠፍቶ የእርሻ ምርት ቢቀንስ እንኳን ሰው በረሃብ የማይሞተው? አስከፊ የረሃብ ዜናዎች የሚሰማባቸው አገሮች በሙሉ ነፃነት የታፈነባቸው አገሮች መሆናቸውስ የአጋጣሚ ጉዳይ ነው? የዝናብ እጥረት ለኢትዮጵያዊ ገበሬ አዲስ ነገር አይደለም። ለምንድነው አንድ ዓይነት ችግር እየተደጋገመብን መላ መፈለግ ያቃተን? "ችግር የመሳካት እናት ናት" የሚለው ብሄል ምነው እኛ ዘንድ አልሰራ አለ? የመጨረሻው ጥያቄ መልስ አጭርና ቀጥተኛ ነው። ችግር የመሳካት እናት የምትሆነው በነፃነት ማሰብ የሚችል ጭንቅላት ሲኖር ነው። በባርነት ጨለማ ውስጥ ያለ ጭንቅላት ለችግሮች መፍትሄ የማፍለቅ አቅም የለውም። እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱ ድኩም ጭንቅላት ችግሮችን ማሸነፍ ሳይሆን ተሸናፊነትን ተቀብሎ ከችግሮች ጋር ተስማምቶና ተወዳጅቶ መኖርን ይመርጣል። ለዚህም ነው የአስተዳደር በደልና ረሃብ ምክንያትና ውጤት ብቻ ሳይሆን እጅና ጓንትም ጭምር የሆኑት። ነፃነት ያለው ሕዝብ ረሃብን እንደሚያሸንፍ ተደጋግሞ የታየ ጉዳይ ነው _ ህንድ የቅርብ ጊዜ ምሳሌያችን ነች። ለዚህም ነው ረሃብን የተፈጥሮ ሚዛን መዛባት ውጤት ብቻ አድርጎ ማቅረብ እውነትን መሸፈጥ የሚሆነው። ረሃብ የብልሹ አስተዳደር ውጤት ነው።

በአገራችን ውስጥ የተንሰራፋው ስር የሰደደ ድህነትና ረሃብም የዘመናት የብልሹ አስተዳደር ውጤቶች ናቸው። ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ጀምሮ የነበረው ብልሹ የምጣኔ ሃብት አስተዳደር አገዛዝ በተቀየረ ቁጥር እየባሰበት መጥቷል። በረሃብ የሚጠቃው ሕዝብ ብዛትም እንደዚያው እየጨመረ መጥቶ ዛሬ 14 ሚሊዮን ሕዝብ እርዳታ ፈላጊ ሆኗል። ችጋር አድማሱን አስፍቶ ቀድሞ በለምለምነታቸው ብቻ ይታወቁ ወደ ነበሩት የደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ መንደሮችም ዘልቋል። አገራችንን የረሃብ ቀጠና ካደረጉ የ19 ዓመታት የወያኔ "የዘርፈህ ብላ" የኢኮኖሚ ፓሊሲ ውጤቶች መካከል አንዳንዱን ለአብነት ያህል መዘርዘር ይቻላል።

1. የወያኔ ቁንጮዎች ራሳቸውን ባለሚሊዮኖች አድርገዋል። እነዚህ በአንድ ጀምበር የበቀሉ ቱጃሮች ከገንዘብ በተጨማሪም የጄኔራልነት፣ የሚኒስቴርነት፣ የክልል ገዢነት፣ እጅግ ቢያንስ የቢሮ ኃላፊነት ሥልጣንን ኪሳቸው ውስጥ ከተዋል። የመንግሥት ሥልጣንና ሃብት ይኸን ያህል የተቆራኙበት ሥርዓት በኢትዮጵያ ኖሮ አያውቅም። የጥቂቶች ያለአገባብና ያለቅጥ መክበር በአንፃሩ ደግሞ የብሃኑን ሕዝብ መደህየት ድህነትን ቀጣይ ያደርጋል።
2. በአቋራጭና በፍጥነት ለመክበር አስተማማኙ መንገድ የገዛ ራስ ጥረትና ታታሪነት ሳይሆን ቅጥፈት፣ አጭበርባሪነትና ሎሌነት ማደር መሆኑን በተግባር ወያኔ እያሳየ ጥሮ ማደርን "ኋላ—ቀር አሠራር" አድርጎታል። በዚህም ምክንያት አድርባይነት፣ ስንፍናና እና ልመና ችግርን የመጋፈጥ አቅማችንን ሰልበውታል።
3. ደኖቻችን ተጨፍጭፈው፣ ለም መሬታችን ተሸርሽሮ በማለቁ የግብርናችን ምርታማነት በእጅጉ ቀንሷል። በዘመነ ወያኔ የደን ጭፍጨፋና የመሬት መሸርሸር በአስደንጋጭ ሁኔታ ጨምሯል። አገሪቷ በፍጥነት ወደ ምድረ በዳነት እየተቀየረች ነው።
4. ገበሬና መሬት ተለያይተዋል፤ አዳዲሶቹ ባላሃብቶች ለፈጣን ኪስ መሙላት እንጂ ለዘለቄታ የአፈር ልማት ፍላጎቱም እውቀቱም የላቸውም። ለም መሬቶች በኢንቨስትመንት ስም በዘመኑ የወያኔ ጉልተኞች በመያዛቸውና እነሱ ደግሞ በተራቸው ለባዕዳን እየሸጡ በመሆኑ ባለሃገሩ ጭሰኝነት እንኳን አጥቶ ለቀን ሠራተኝነትና ልመና ተዳርጓል። በዚህም ምክንያት ገበሬው እንኳንስ ትልቁን የአየር መዛባት ትንሿንም የዋጋ ነውጥ መቋቋም እስከማይችልበት ደረጃ ተዳክሟል።
5. በዘር በተመሰረተ ክልላዊ ድንበር ሳቢያ ኢትዮጵያዊያን ገበሬዎች በአገራቸው ውስጥ ተዘዋውረው መሥራት አልቻሉም። ከሰሜን ወደ ደቡብ ከተሰደደ የአገራችን አርሶ አደር ይልቅ ለቻይና ገበሬ መሬት ማግኘት ይቀለዋል። እንዲያውም ኢትዮጵያዊው ገበሬ በዱላ ሲባረር፤ የቻይናው ገበሬ ብድርና ማበረታቻዎች ይሰጠዋል።
6. ኢትዮጵያዊያን ገበሬዎች ድርቅን መቋቋም ስለሚችሉ ሰብሎች ወይም የአስተራረስ ዘዴዎች ማሰብ፣ መመራመርና መፈተሽ አይችሉም። አዲስ ነገር መሞከር የግብርና ፓሊሲን በመቃወም ወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር ነው። ፈጠራ በእንዲህ ዓይነት ሥርዓት ውስጥ አያድግም።
7. ፋይዳ ያለው የስነ ሕዝብ ፖሊሲ ባለመኖሩ የሕዝብ ብዛት አሻቅቧል። እንደ ኢኮኖሚው ሁሉ ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ብዛት ሊቆጣጠር የሚሞክረው ቢሮ ውስጥ ቁጭ ተብሎ በሚደረግ የቁጥር ምርጫ ነው። የስታተስቲክሱ ባለሥልጣን ቁጥራችንን በትክክል ሊነግረን ባይፈልግም እንኳን ረሃብ መብዛታችንን እየነገረን ነው።

እነዚህና የመሳሰሉት ጭብጦችን በማንሳት የረሃቡ መሠረታዊ ምክንያት ወያኔ እንጂ ተፈጥሮ አለመሆኑን አስረግጠን እንናገራለን። ሕዝባችን በነፃነት ማሰብ፣ መመራመር፣ መፈተሽ ቢችል ኖሮ ረሃብን ማጥፊያ ብልሃት ማግኘት ባላቃተውም ነበር። ወደፊትም ቢሆን ተፈጥሮ እኛ እንደፈለግናት አትሆንም፤ መተማመኛችን የሰው ልጅ ወሰን የለሽ የፈጠራ ችሎታና ችግሮችን የመፍታት አቅም ነው። ለዚህ ችግሮችን በልጦ መገኘት ያስፈልጋል። ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሁሌ ከችግሮች በታች ሆኖ የእሱን ፈቃድ እንዲያሟላ ይፈልጋል፤ ለዚህም ነው ባርነትን ያወጀብን። እኛ ደግሞ የችግሮቻችን ቁንጮ ራሱ ወያኔ ነው የምንለው ለዚህ ነው። ወያኔን ሳናስወግድ ድህነትንና ረሃብ እናስወግዳለን ማለት ዘበት ነው።

ድህነት የወያኔ ዋነኛ የገቢ ምንጭ ስለመሆኑ በዚህ በፊትም በተደጋጋሚ ያነሳነው ጉዳይ ነው። ረሃብና ችጋርም እንደዚያው የወያኔ "ጪስ አልባ" እንዱስትሪዎች ናቸው። ሕዝባችን ተራበ ማለት የወያኔ ኩባንያዎች ሥራ አገኙ ማለት ነው። ወያኔ የራሱን "መንግሥታዊ ያልሆኑ" ድርጅቶች የማጠናከርና ገለልተኞቹን የማቀጨጭ ሥራ የጀመረው አራት ኪሎ እንደደረሰ ቢሆንም ረሃቡ በጨመረ መጠን እሱም "ገበያውን" ብቻውን ለመቆጣጠር የሚያደረገው ልብ ይሏል።

ረሃብ ያለፉት ሶስት ተከታታይ አገዛዞች የባህሪይ ተመሳሳይነትንም አጉልቶ አሳይቶናል። የሶስቱም አገዛዞች ቁንጮዎች ሰለረሃብ ተጠይቀው የሰጡት ትዕቢት የተሞላበት ምላሽ በሚገርም መጠን ተመሳሳይ ቢሆኑም የመለስ ግን ከሁሉ ይብሳል። መለስ ከቀደሙት ሁለቱ በባሰ እየለመነ ይሳደባል፤ እየተሳደበ ይለምናል። ስለ ኢኮኖሚ እድገት ሰፊ ገለፃ ከሰጠ በኋላ ንግግሩን በእርዳታ ልመና ይደመድማል። በመለስ አመክኖ ተፈጥሮ፣ ለጋሽ አገራት፣ የእርዳታ ድርጅቶች እና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለረሃቡ ተጠያቂ ናቸው። እውነታው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። ለወገኖቻችን መራብ ተጠያቂው ወያኔ ነው። ወያኔን ሳናስወግድ ድህነትና ረሃብን ከኢትዮጵያ ምድር መንቀል አንችልም።

በወያኔ አገዛዝ በረሃብ ለሚጠቃው ወገናችን መድረስ የምንችለው፤ የረሃቡን መሠረታዊ ምክንያት የሆነውን የወያኔን አገዛዝ አስወግደን ፍትህና ነፃነት የሰፈነባትን፤ ፈጠራ የተስፋፋባትን ኢትዮጵያን ስንገነባ ብቻ ነው። ጊዜ የለም .... ረሃብ ጊዜ አይሰጥም። የወገኖቻችንን ሕይወት ለመታደግ በአንድነት እንነሳ።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

ማስታወቂያ

የግንቦት 7 ድምጽ የአድማጮቹን አስተያየት በስልክ ጭምር ለመቀበል እንዲያስችለው  አንድ የስልክ መስመር ከፍቶአል ። ስለዚህ ስለፕሮግራማችን አስተያየት ሲኖራችሁ በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661 ልትደውሉልን የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ኑር ወይም ሙት

ኤሎን - ከጎፋ ሰፈር

ሰሞኑን በግንቦት 7 ድምጽ ደጋግሞ የቀረበው ዜና ለዚህ ጽሁፍ መነሻ ሆነ። በርግጥ የዜናው ተደጋግሞ መተላለፍ አይደለም ትኩረቴን ይበልጥ የሳበው፤ የችግሩ አሳሳቢነትና ያገኘው ትኩረት አለመመጣጠን እንጅ። ለነገሩ አይፈረደም፣ ትኩረታችንን የሚበታትኑ በርካታ ችግሮች በየቀኑ የወለዳሉ። “ዛሬ እንዲህ ሆነ፣ ወያኔ እንዲህ አደረገ” ስንል፣ ነገ ሌላ ችግር ብቅ ይላል። የምርጫ 97 ችግር በቅጥጡ ሳይፈታ፣ የሶማሊያ ጦርነት መጣ፣ ይህም በደንብ ሳይቋጭ፣ የኦጋዴን ችግር ተከሰተ፤ በመሀሉ ደግሞ የወ/ት ብርቱኳንና የቴዲ አፍሮ እስር ትኩረታችንን ሳበው። ሰሞኑን ደግሞ ለሱዳን የሚሰጠው ሰፊ መሬት እንቅልፍ እያሳጣን ነው። ሌሎች መለስተኛ ችግሮችም እንዲሁ ሃሳባችንን ከመበታተን አልተቆጠቡም፤ ረሀቡ፣ ሙስናው፣ የብሄር ጭቆናው፣ የእነጄ/ል ተፈራ ማሞ እስር ወዘተ። በጣም የሚገርመው ሁሉም ችግሮች “ወያኔ ሰራሽ” መሆናቸው ነው። ወያኔ ችግሮችን እየቀፈቀፈ፣ የእኛንም ሀሳብ እየበታተነ ለ 19 አመታት ገዝቶናል። የሃሳባችን መበታተን በወያኔ ላይ የተጠናከረ ትግል እንዳናደርግ ካደረጉን ምክንያቶች አንዱ ነው። የሰሞኑ “ወይ’ን ለመኖር” ፖሊሲም በዚህ ስሌት ታስቦ የተፈበረከ ነው። ይህ ፖሊሲ በአገር ቤት ትልቁ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኗል፤ ምክንያቱም ግልጽ ነው፤ የእያንዳንዱን የመኖርና ያለመኖር እጣፋንታ የሚወስን አደገኛ ፖሊሲ በመሆኑ ነው ። ማን በአገሩ መኖር እንዳለበት ፣ ማን መኖር እንደሌለበት የሚወስን ፖሊሲ ነው። ፖሊሲው በወያኔው ህገ መንግስትና በአለማቀፍ ህግጋት የሰፈሩትን “የመኖር፣ ስራ የመስራት፣ በእኩል የመታየትና የመደራጀት” መሰረታዊ መብቶችን የሚቀብር ነው።በኢትዮጵያ ውስጥ ለመስራት ፣ ሰርቶም ለመኖር የግድ በወያኔነት የጸበል ውሀ መመታት ያስፈልግል፤ አመና መጠመቅ ብቻ ሳይሆን ሳያምኑም ሳያውቁም መጠመቅ ይችላል። ተፈላጊው ነገር የጥምቀት ካርዱን መያዙ ነውና።

“ወይ’ን ለመኖር” ፖሊሲ ሁለት ገጽታዎች አሉት። አንዱ ገጽታ በገጠር ያለውን ህዝብ የሚመለከት ነው። በገጠር ያለው ህዝብ አንድም አምራች ነው፣ ሌላም በዳረንጎት የሚኖር ነው። አምራች የሆነው ገበሬ በቀጥታ ከወያኔ ወይም ከእርዳታ ድርጅቶች ዳረንጎት አይቀበልም፣ ስለዚህም ወያኔ ይህን ሀይል በቀጥታ በሆዱ ሊቆጣጠረው አይችልም፤ ቁጥጥሩ የሚደረገው በተዘዋዋሪ መንገዶች ነው። ለወያኔ ያላደረ አምራች ገበሬ ምርጥ ዘር አያገኝም፣ ግብር በወቅቱ አልከፈልክም ተብሎ ይታሰራል፣ ሽፍታ ታደራጃለህ ተብሎ ይገረፋል፣ የተቃዋሚ ደጋፊነህም ተብሎ ይገደላል። አንድ ምሳሌ ልስጣችሁ፣ ከግንቦቱ 97 ምርጫ በሁዋላ መለስ ዜናዊ ወደ ጎጃም አካባቢ ሄዶ ነበር። ከመለስ ጉዞ ቀደም ብሎ ገበሬዎች በካድሬዎች እየተጠሩ “ቅንጅትን የመረጥነው በስህተት ነው እያላችሁ ተናገሩ” ተብለው ነበር። አንዱ ገበሬ ግን “አሻፈረኝ” አለ፤ እንዲያውም የአካባቢውን ተወላጆች አስተባብሮ በወያኔዎች ላይ ተቃውሞ አስነሳ። ብዙም ሳይቆይ ግን የወያኔ የቅጣት በትር በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ ማረፍ ጀመረ። ያ ገበሬም ወደ አማራው ክልል ዋና ከተማ፣ ባህርዳር፣ ሄዶ ታሰረ። መታሰሩ አይደለም የገረመኝ። ወደ እስር ቤት ከመላኩ በፊት ወያኔ በርካታ ካድሬዎቹን ልኮ እንደእባብ አስቀጠቀጠው። በሰው ልጆች ላይ ይደርሳል ተብሎ የማይታሰብ ግፍ ደረሰበት። ከሁለት አመት እሰር በሁዋላ ያ ግዙፍ ሰውነቱ እንደጨው ሟሙቶ፣ እጆቹና እግሮቹ ሽባ ሆነው፣ በበሽታ ላይ በሽታ ሽምቶ ተለቀቀ። ወደ ቀየው ሲመለስ የአካባቢው ህዝብ የጀግና አቀባበል አላደረገለትም። በጣም ጥቂቶች ጨለማን ተገን አድርገው “ እንኳን እግዜር አሰፈታህ” ብለውታል። በሁዋላ እንደተረዳሁት የአካባቢው ህዝብ “ ቅንጅትን የመረጥነው በስህተት ነው፤ መሪያችን ያዲግ ነው፣ ጌቴን አንከተልም “ ብለው በምህላ አረጋግጠው ነበር (ጌቱ የዚሁ እስረኛ ስም ነው)። ታዲያ መለስ ዜናዊ ወደ አካባቢው ሲሄድ ያ በምህላ የተያዘ ህዝብ “እንደጉድ ወጥቶ ተቀበለው”። የጎጃም ህዝብም “ተሳስተን ነበር” ብሎ በመናገሩ ይወርድበት የነበረውን መአት አሳለፈ ተባለ። ሰልፉም በቴሌቪዥን ቀርቦ ታየ።መለስም ራሱን አታለለ። አሁን ያ ኩሩ ገበሬ ይኑር ይሙት አላውቅም።

በሌላ በኩል ግን በእርዳታ የሚኖረው ገበሬ እንደ አምራቹ ገበሬ ትንሽ እንኳን ለማንገራገር አይችልም። የጌቴ እድል የለውም ማለቴ ነው። ያለው ምርጫ አንድም “የወይ’ን ለመኖር” ፖሊሲን ተቀብሎ የምትሰፈርለትን ጥሬ እየቆረጠመ መኖር ነው አልያም መሞት ወይም መሰደድ ነው። ይህ ምርጫ ቀርቦላቸው “ ወይ’ን ለመኖርን” የተቀበሉ፣ ወያኔ ራሱ ባመነው፣ 7 ሚሊዮን ዜጎች አሉ። ወያኔ የሴፍትኔት ዜጎች ይላቸዋል፤ ትክክለኛ ስያሜያቸው ግን “ የወይ’ን ለመኖር” ዜጎች ነው። እነዚህ ገበሬዎች ወያኔን ካልደገፉ ሞት እንደሚጠብቃቸው ያውቃሉ። ስለዚህ ሁሌም፣ ቢያንስ በአፋቸው፣ ለመለስ ዜናዊ እድሜ እየለመኑ ይኖራሉ። ወያኔ “የወይ’ን ለመኖርን” ፖሊሲ በገጠር እየተገበረ ያለው በዚህ መንገድ ነው።

ሁለተኛው የዚህ አደገኛ ፖሊሲ ገጽታ ከተሜውን የሚመለከት ነው። በከተማ ያለው የ”ወይ’ን ለመኖር” ፖሊሲ አላማ፣ እንደገጠሩ ሁሉ፣ ህዝቡን “ማወየን” ቢሆንም በአተገባበር ስልቱ ከገጠሩ በመጠኑም ቢሆን የሚለይበት ነገር አለው። በገጠሩ ያለው ማህበረሰብ በአብዛኛው የመንግስት ተቀጣሪ ሳይሆን በግል ለፍቶ አዳሪ ነው። በከተሞች ያለው ህብረተሰብ ደግሞ በግል ድርጅቶች ውስጥ ተቀጣሪ ካልሆነ ወይም በግልስራ ላይ ካለተሰማራ ወይም ስራ አጥ ካልሆነ የመንግሰት ተቀጣሪ ነው ። አሁን ባለው መረጃ መሰረት በግል ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው ከሚሰሩት ዜጎች ቁጥር ይልቅ በመንግስት መስሪያቤቶች ተቀጥረው የሚሰሩት ዜጎች ቁጥር ይበልጣል። በግል ድርጅቶች ያለውን የሰራተኛ ብዛት ብናይ እንኳ፣ ዋነኞቹ ቀጣሪዎች የወያኔ ድርጅቶች ወይም የወያኔ ደጋፊ ድርጅቶች ናቸው ( እነ ኢፈርትንና የአላሙዲን ድርጅቶችን ይጠቅሷል)። ይህ ማለት ወያኔ አብዛኛውን ቅጥር ሰራተኛ የሚቆጣጠርበት ሀይል አለው ማለት ነው።

በዜናዎቹ እንደምንሰማው በርካታ የመንግስት ሰራተኞች ከስራቸው እየተባረሩ ነው። ወያኔ ከፈረንጆቹ ጋር እንዳይጣላ የተቋማት ለውጥ፣ በእንግሊዝኛው ምህጻረ ቃል “ቢፒአር”፣ እያደረኩ ነው ይበል እንጅ በትክክል እያደረገ ያለው ደጋፊዎቹን ደጋፊዎች ካልሆኑት በመለየት የመቅጠርና የማባረር ዘመቻ ነው። ባለኝ መረጃ መሰረት በርካታ ዜጎች፣ በተለይም ባለሙያ የሆኑት፣ አንወይንም በማለታቸው ከስራ ተባረዋል። የትምህርት ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑት ደግሞ አማራጭ በማጣት መወየንን እየመረጡ ናቸው። ከጽዳት ወደ ጸሀፊነት ለመሸጋጋር አቋራጩ መንገድ መወየን መሆኑን ሁሉም የሚመሰክረው ነው። አንዳንዴ ብዙ ጽዳቶች ይበዙና ለጸፊነት ያለው ቦታ አንድ ብቻ ይሆናል። ያኔ ከወያኔነት በተጨማሪ ጥሩ ዳሌም ግምት ውስጥ ይገባል።

በጣም የሚያሳዝነው አዳዲስ የኮሌጅ ምሩቃንም ሳይቀሩ ካልወየናችሁ ስራ አታገኙም መባላቸው ነው። ብዙ ወጣቶች ስራ ይዘው ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳትና ራሳቸውን ለማሻሻል የነበራቸው ህልም ከፊታቸው በተደቀነ ከባድ ፈተና እየተነነ ነው።ወያኔነት ከዲግሪ የበለጠ ዋጋ አለው። “ወይ’ን ለመኖርን” አንቀበልም ያሉና በግል ድርጅቶች የመቀጠር እድሉን ያላገኙ ወጣቶች በብስጭት ጫት ቃሚዎች ጠጪዎች፣ ወንጀል ሰሪዎች ወዘተ ሆነዋል። ከቅርብ አመታት በፊት ለጉብኝት ወደ ናዝሬትና ባህርዳር ከተሞች ሄጄ ነበር። በከተማው ያሉ አብዛኞቹ ወጣቶች ጥርሳቸው በጫት፣ ከንፈራቸው በሲጋራ ደርቆ ሳይ በእጅጉ ነበር የደነገጥኩት። በእነዚህ ከተሞች ካሉት ሄቴል ቤቶች ቁጥር ይልቅ የጫት ቤቶች ቁጥር ይበልጣል ብል ያጋነንኩ አይመስለኝም። ጫት ቃሚዎች ደግሞ አብዛኞቹ “ወይ’ን ለመኖር” ያገለላቸው ስራ አጥ ወጣቶች ናቸው።

በከተማችን ያለው የጥቅምት ወግ ይህ ነው። ከስራ የተባረረው “ወይን ለመኖር”ን አልቀበልም ብየ ተባረርኩ ሲል ስራ ፈላጊው ደግሞ “ወይ’ንና እንቀጥርሀለን” አሉኝ ” ይላል። በመንገድ ላይ ፣ባልሳሳት፣ በየሶስት ሜትሩ ቆመው የሚለምኑትን ወዛም የኔቢጤዎች ጠጋ ብላችሁ ስትጠይቋቸው የሚነግሯችሁ “በ ቢፒአር ተባርሬ ቤተሰቦቼን የማበላቸው አጣሁ” የሚል ነው። ቢፒአር ምንድን ነው? ስትሉዋቸው ደግሞ “ ያው “ወይ’ን ማለታቸው ነዋ” ይሉዋችሁዋል።

በዚህ ፖሊሲ ዜጋው በአገሩ የመኖር፣ የመስራት፣ የመደራጀት ወዘተ ነጻነቱን በጠራራ ጸሀይ እየተገፈፈ ነው። በርግጥ ገፈፋው ከተጀመረ ቆይቷል። አሁን ግን ልንሸከመው ከምንችለው በላይ ሆኖብናል። በአለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 23 መሰረት ማንኛው ዜጋ በነጻነት የመስራት፣ የመረጠውን ስራ የመስራት፣ ተስማሚና ፍትሀዊ የስራ ከባቢ የማግኘት መብቶች እንዳሉት ተደንግጓል። በዚሁ ድንጋጌ ላይ የመኖርና የመደራጀት መብቶችም ሰፍረዋል። ወያኔ የሚዘምርለት ህገመንግስትም ተመሳሳይ ነገር ይናገራል። እነዚህ ሁሉ ህግጋት ባሉበት ነው እንግዲህ ወያኔ በአገራችን ላይ የመኖርና ያለመኖር ምርጫ የሚሰጠን።

አሁን ወያኔ የጀመረው አሰራር አደገኛነቱ አያጠያያቅም። ዜጎች እርስ በርስ እንዲጠላሉ የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን አንድ አምባገነን አገዛዝ ለዘላለም በስልጣን ላይ እንዲቆይ የሚያደርግ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ፣ በተለይ ጸጉሩን በመንጨት ቁጭቱን የሚወጣው ወጣት ክፍል፣ ይህን አደገኛ አካሄድ ማስቆም ይጠበቅበታል። ወያኔን ታግለን ካላስወገድነው፣ መቼውንም ከችግር አዙሪት አንወጣም።

## በኢትዮጵያ ያለው የውሀ አቅርቦት በተለይ በገጠራማ አካባቢዎች እጅግ አስከፊ እንደሆነ ተገለጸ

ከሰማንያ ከመቶ በላይ ኢትዮጵያዊያን የእለት ተለእት መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ለሟሟላት የሚያስፈልጋቸውን ንጹህ ውሀ እንደማያገኙ ታውቋል። ዩኒሴፍ ስር የሰደደውን የውሀ ችግር ለማቃለል አንዳንድ እርምጃዎች እየወሰደ እንደሆነ የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

ወያኔ በሚቆጠጣጠራቸው የመገናኛ ብዙሀን የኢትዮጵያን ህዝብ እጅ እጅ እስከሚለው በግድ ከሚግተው ወሬ አንዱ የእገሌ ወረዳ ህዝብ የንጹህ ውሀ አቅርቦት ተጠቃሚ ሆነ እና የቧንቧ ውሀ ተዘረጋለት እንደሆነ ይታወቃል።

መለስ ዜናዊ በጫት ፈረስ እየጋለበ ሀገሪቱን ቤተ ሙከራ ማድረጉ ግልጽ ነው። ከእነዚህም በዋነኛነት የሚጠቀሰው በሀገሪቱ ያለውን የዝናብ እጥራት ለመቅረፍ ትልልቅ ጉድጓዶች ቆፍሬ ውሀ አቁራለሁ ብሎ ያፈሰሰው የሀገር ንብረት እና የታቆረው ውሀ ለወባ ትንኝ መከማቻ አመቺ በመሆኑ ያለቀው የገበሬ ብዛት ነው።

ለባለፉት አስራ ስምንት አመታት ሀገሪቱን ረግጦ የገዛት ወያኔ አምጥቼዋለሁ እያለ የምፎልልበት የውሸት እድገት ከእውነታው ጋር ጨርሶ መስማማት እያቃተው እየመጣ እንደሆነ የተለያዩ አለምአቀፍ ድርጅቶች የሚያቀርቡት በጥናት ላይ የተመሰረተ ዘገባ እርቃኑን እያስቀረው እንደሆነ ግልጽ ነው።ከምንም በላይ ደግሞ በግፍ ሰንሰለት የታሰረው የኢትዮጵያ ህዝብ ልማቱም ሆነ አምጠተንልሃል የሚሉት ዕድገት በመገናኛ ብዙሃን ወያኔ የሚያሰራጨው ርካሽ ፕሮፓጋንዳ ብቻ እንደሆነ ከተገነዘበ ውሎ አድሮአል።

በቅርቡ አንድ የተቋዋሚ አባል "ኢትዮጵያ እያደገች ያለችው ቴሌቭዥን ውስጥ ነው" ብሎ ወያኔ በከንቱ የሚነዛውን ፕሮፓጋንዳ በደንብ የሚያሳይ ንግግር ማድረጉ ይታወሳል።

## በመከላኪያ ሚንስቴር የመንግሥት . . . ከገጽ 1 የዞረ

በርሀብና በችግር ከሚሰቃየው የኢትዮጵያ ህዝብ እየተነጠቀ በግብር ስም የሚሰበሰበው ገንዘብ፣ ለወያኔ ታማኝ ለሆኑ ጥቂት የትግራይ ተወላጅ ጄኔራሎች ሀብት ማካበቻና መቅበጫ መሆኑ በእጅጉ እንደሚያሳዝናቸው የሚናገሩት የሚኒስቴሩ ቅጥር ሰራተኞች፣ ሁኔታውን እያዩ መታገስ ባለመቻላቸው አንዳንዶች ራሳቸውን ለማጥፋት እስከመነሳሳት መድረሳቸውን ተናግረዋል።

አብዛኛው የመከላከያ ሰራዊት አባላት ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳት በማይችሉበት ደረጃ ውስጥ እያሉ፣ እነኚህ ጥቂት የወያኔ ጄኔራሎች ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ ሚሊየነሮች መሆናቸው በሰራዊቱ ውስጥ ለሚታየው ሽኩቻ አንዱ መንስኤ መሆኑንም የመከላከያ ሰራተኞች ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ አገሩ በዘረኝነት በተሰባሰቡ ጥቂት ሽፍቶች ስትዘረፍ ዝም ብሎ መመልከት እንደሌለበት፣ በተለይም የመከላከያ ሰራዊቱ አባላት የተቃውሞ ክንዳቸውን በደሙ በሚነግዱት አመራሮቹ ላይ ማንሳት እንዳለባቸው የግንቦት 7 ንቅናቄ በተደጋጋሚ እያሳሰበ ይገኛል።

## ወያኔ በየአመቱ ለሲቪል ሰራተኞች . . . ከገጽ 1 የዞረ

በተያያዘ ዜናም ወያኔ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል በሚል ሰበብ ወላጆች፣ ተማሪዎችና መምህራን አንድ የኮንትራት ስምምነት እንዲፈርሙ እያደረገ መሆኑን የደረሰን መረጃ አመልክቷል። የኮንታራት ስምምነቱ የትምህርት ጥራት ለመጠበቅ ይበል እንጅ የትምህርት ጥራትን ለመጠበቅ የሚረዱ ነገሮች በኮንትራቱ ውስጥ አልተቀመጡም። መምህራንን በመጠየቅ ያገኘነው መረጃ እንደሚያሳየው ወያኔ ወላጆችን የሚያስፈርመው ተማሪዎች በምርጫው ወቅት ራሳቸውን በጥናትና በፈተና በመወጠር ለምርጫው ትኩረት እንዳይሰጡ ለማድረግ ነው። በዚህ የኮንታራት ስምምነት ተማሪዎች በግንቦቱ 97ቱ ምርጫ ወቅት እንዳሳዩት አይነት ተቃውሞ ቢያሳዩ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት እንደሚባረሩም ለማወቅ ተችሎአል።

## የኦጋዴን ነጻ አውጭ ድርጅት . . . ከገጽ 1 የዞረ

ተብሎ ከሚጠራው የሱማሊያ ታጣቂ ቡድን ጋር ቁርኝት እንዳለው አድርጎ ማስወራቱ ወያኔ አሁን ያለበትን የማንነት ቀውስ ያሳያል የሚለው ኦብነግ፣ ለወያኔ እርዳታ የሚለግሱ አለማቀፍ መንግስታት ከወያኔ የተሻለ የስለላ ተቋማት የላቸውም ብሎ እነሱን ለማታለል አስቦ የፈጠረው ተንኮል ከሆነ፣ አገዛዙ ትልቅ አደጋ ውስጥ ገብቷል ማለት ነው ሲል ተሳልቋል።

የአምባገነኑ መለስ ዜናዎ አገዛዝ የኦብነግ ተዋጊዎችን በሁለት ሳምንት ውስጥ ድምጥማጣቸውን እናጠፋቸዋለን ብሎ ከሁለት አመት በፊት በይስሙላ ፓርላማው ፊት መናገሩ የሚታወስ ሲሆን፣ እነሆ ከ 2 አመት በሁዋላ ቢሆን አካባቢው ትልቅ የጸጥታ ችግር ያለበት ነው። የወያኔ ባለስልጣኖች ከከተሞች አልፈው ወደ ገጠር ዘልቀው መግባት እንደማይችሉ መረጃዎች የሚጠቁሙ ሲሆን፣ አብዛኛው የኦጋዴን ክልልም በኦብነግ ተዋጊዎች የተያዘ መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል።

በተያያዘ ዜናም ከኦጋዴን ሁኔታ የምንማራቸው በራካታ ቁምነገሮች እንዳሉ አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ። በንጽጽር አነስተኛ ሀይል ያላቸው የኦብነግ ሀይሎች የወያኔን ጦር ለአመታት መፈናፈኛ አሳጥተው ማቆማቸው፣ የወያኔ ጦር ሀይል መዳከሙን፣ የወያኔ ጦር ውስጡ የተቦረቦረና ለውጊያ ዝግጁ ባልሆኑ ስልቹ ወታደሮች የተሞላ መሆኑን ያሳያል የሚሉ ወገኖች አሉ። የግንቦት 7 ንቅናቄ በተባበረና በተቀናጀ ህዝባዊ ትግል ፤ ላለፉት 18 ዓመታት የአገሪቱን ከፍተኛ የፖለቲካ ስልጣን ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር ከዘር ፍጅት እስከ አገር ክህደት ወንጀል የፈጸሙትን ጥቂት የወያኔ መሪዎችንና በዘረፋ ሃብት ያካበቱትን ቤተሰቦቻቸውን ጭምር ለፍትህ ለማቅረብ የሚደረገውን ሁለገብ ትግል አጠናክሮ እንደሚቀጥል ለወዳጅም ለጠላትም በመግለጽ ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል።

## ወያኔ ለም የእርሻ መሬቶችን ሽያጭ አጧጡፎአል። አላሙዲን 500ሺ ሄክታር ሊሰጠው ነው።

ሥልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ በየአመቱ እየጨመረ የመጣውን የረሃብተኛ ቁጥር ለመቀነስ ምንም አይነት ተግባራዊ እርምጃ ሲወስድ የማይታየው የወያኔ አገዛዝ በአለም አቀፍ የምግብ እርዳታ ህይወቱን የሚያቆየውን ከ14 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን ስቃይ ወደጎን በመተው በአገሪቱ እየተመረተ ወደውጭ ለሚላክ የእርሻ ምርት ለም መሬታችንን ለውጭ ባለሃብቶች የመሸጥ ጥድፊያውን ቀጥሎበታል፡፡ ሳውዲ ስታር የግብርና ልማት በሚል ስያሜ በነሀሴ 13፣2001 አመተ ምህረት የተመዘገበው የሼህ አላሙዲን ድርጅት ይህንን የወያኔ የዘረፋ ሩጫ የከፈተውን ዕድል ለመጠቀም ካሰፈሰፉት ባለሃብቶች አንዱ በመሆን ከፍተኛ መጠን ያለው መሬት ለማጋበስ ማቀዱ ታውቋል።

ወያኔ የአገዛዝ እድሜው ከማጠሩ በፊት የአገሪቱን አንጡራ ሃብት ጠቅልሎ በመሸጥ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያደርገውን ሩጫ ተግባራዊ እንዲያደርግ እያገዘው ያለው ሼህ አላሙዲን ከ500 (አምስት መቶ) ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በተወሰኑ አመታት በቁጥጥሩ ስር ለማስገባት እንዳሰፈሰፈ እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁለት መቶ ሺህ ሄክታር መሬት በእጁ እንደሚያስገባ ተገልጿል።

የኢትዮጵያን ለም መሬት ተጠቅሞ ለሳውዲ አረቢያ እህል አቅርቦ በሀገሪቱ ኪሳራ ትርፍ የማጋበስ እቅድ ያለው የአል አሙዲን አዲሱ ድርጅት፤ በጋምቤላ አልዎሮ የተባለ ቦታ ላይ የተሰጠውን መሬት በደርግ ጊዜ በተሰራ ግድብ በነጻ እየተጠቀመ እንዲሰራ እንድተፈቀደለት ታውቋል። በከፍተኛ መጠን እየተቸበቸበ ያለው የኢትዮጵያ መሬት ሳያንስ በህዝብ ንብረት የተሰሩ ግድቦችን ባእዳን በነጻ እንዲጠቀሙበት መፍቀድ ትልቅ ወንጀል ነው ተብሎአል።

በከባድ መስእዋነት ተከብሮ የቆየውን የኢትዮጵያን ምድር ለባእዳን በፍጹም ጻረ ኢትዮጵያ ስሜት በከፍተኛ ቢሊዎን ዶላሮች እየቸበቸበ ያለው ወያኔ፤ ሀገሪቱን በቁሟ ሸጦ ሳይጨርሳት አፋጣኝ መፍትሄ ካልተበጀ በቀር በቅኝ ግዛት እና በአፓርታይድ ዘመን መሬታቸውን በባዕዳን ተነጥቀው ዛሬ በገዛ አገራቸው የጭሰኝነት ኑሮ እየገፉ እንዳሉ የደቡብ አፍሪካ አገሮች እንደምንሆን ልንጠራጠር አይገባም የሚሉ በርካታ ዘጎች ናቸው። የግንቦት 7 ንቅናቄ በተባበረ ትግል ወያኔን በሃይል ከስልጣን የማባረሩን አስፈላጊነት የሚሰብከውና ለተግባራዊነቱ ተግቶ የሚሰራው ከዚህ የወያኔ ጻረ አገር አቋም በመነሳት እንደሆነ በተደጋጋሚ ገልጾአል።

## በአዲሱ "ወይ'ን ለመኖር" ፖሊሲ ህዝቡ . . . ከገጽ 1 የዞረ

አለመቀበላችሁን የሚያረጋገጥ ቅጽ በቅድሚያ መሙላት አለባችሁ" እንደተባሉ የተናገረው ዘጋቢያችን፣ ብዙዎች በሁኔታው በመገረም ፎረሙን ሳይሞሉ መመለሳቸውንም ገልጿል። አንዳንዶች ደግሞ ወያኔ ፊታችንን እንጅ ልባችንን ማግኘት አይችልም በሚል እምነት ፎረሙን መሙላታቸውን ገልጿል።

ይህ አይነቱ አሰራር በሁሉም መስሪያቤቶች ተግባራዊ እየሆነ መገኘቱን ተዘዋውሮ የተመለከተው ዘጋቢያችን፣ በርካታ ወጣቶች ለሆዳችን ስንል ህሊናችንን አንሸጥም፣ በማለት ተቃውሞዋቸውን እያሰሙም እንደሚገኙ ተናግሯል። በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ ውስጥ ያለው ትልቁ የመነጋገሪያ አጀንዳ "ወይ'ን ለመኖር" የተባለው ፖሊሲ መሆኑ ሲታወቅ፣ ህብረተሰቡም በወያኔ ድርጊት በእጅጉ እያዘነና ብስጭቱንም በመግለጽ ላይ መሆኑን ለመረዳት ተችሎአል።

ብዙዎቹ አዳዲስ የዩኒቨርስቲ ተመራቂዎች በወያኔ አሳፋሪ ድርጊት ተስፋ በመቁረጥ ስደትን እንደአማራጭ እየወሰዱ መገኘታቸውን የደረሰን ዘገባ የሚያመልክት ሲሆን፣ አንዳንድ ወጣቶች ግን የነጻነት ሀይሎችን በመቀላቀል አገዛዙን ለመፋለም ወደ ጎረቤት አገሮች በመሄድ ላይ ናቸው። በአለፉት ጥቂት ወራት ብቻ በርካታ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች ወደ ጎረቤት አገሮች የተሰደዱ ሲሆን፣ ብዙዎችም ከነጻነት ሀይሎች ጋር ግንኙነቶችን መጀመራቸውን ለማወቅ ትችሎአል።

ወያኔ በየቀኑ ከህዝብ የሚደርስበት ተቃውሞና መገለል እጅግ እያስጨነቀው እንደመጣ የሚናገሩት አስተያየት ሰጪዎች በበኩላቸው፣ አሁን የጀመረው "ወይ'ን ለመኖር" ፖሊሲ ዞሮ ዞሮ ራሱን እንደሚጎዳው የተለያዩ አገሮችን ልምዶችን በመጥቀስ ተናግረዋል። አምባገነን መንግስታት ምንጊዜም መጨረሻቸው እንደማያምር የሚናገሩት አስተያየት ሰጪዎች፣ አሁን በስልጣን ላይ ያሉት የወያኔ መሪዎች ከስልጣን ሲወገዱ ዛሬ ተገደው አባል የሆኑት ወጣቶች ነገ ያለማንም ግፊት በቅድሚያ በወያኔ መሪዎች ላይ የሚነሱት እነሱው ይሆናሉ ብለዋል።

ግንቦት 7 የወያኔን "ወይ'ን ለመኖር" ፖሊሲ አጥብቆ ሲያወግዝ መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን፣ ወያኔን በተባበሩት ክንድ አሽቀንጥሮ በመጣል ብቻ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት እንደሚቻል በጥቅብ አምኖ ትግል በማካሄድ ላይ መሆኑ ይታወቃል።


# የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

## የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661